# የደብሊን 3 የስምምነት ደንብ



የደብሊን 3 የስምምነት ደንብ ዓላማ፣ የጥገኝነት ጥበቃ ሂደቶችን በቀጥታ የማግኘት እና የአለም አቀፍ ጥበቃ ማመልከቻን ስምምነቱን በፈረሙ በአንድ  የአውሮፓ አባል አገር ብቻ መመርመር ነው ። የስምምነት ደንቡ የአለም አቀፍ ጥገኝነት ማመልከቻን የመመርመር ኃላፊነት ያለበትን አባል ሀገር ይለያል ::

ሀላፊነቱን የሚወስደው አገር የትኛው እንደሆነ የሚወሰነው ከታች በቅደም ተከተል የተቀመጡትን መመዘኛዎች መሰረት በማድረግ ነው ።

- ቤተሰባዊ ትስስር፣
- አባል በሆነ አገር በቅርብ ጊዜ የተሰጠ ቪዛ ወይም የመኖሪያ ፍቃድ እንዲሁም
- አመልካቹ ወደ አውሮፓ ህብረት አገር የመጣው በህጋዊ ወይም በህገወጥ መንገድ ከሆነ።

## የደብሊን 3 የስምምነት ደንብ ምንድነው ?

የደብሊን 3 የስምምነት ደንብ ስምምነቱን ከፈረሙት የአውሮፓውያን አገራት ውስጥ ማመልከቻዎን የትኛው አገር የመመርመር ኃላፊነት እንዳለበት ይወሰናል ።

የዓለም አቀፍ ጥገኝነት ማመልከቻ ሲያቀርቡ፣ የእርስዎንና ከ14 አመት በላይ የሆኑ የቤተሰብዎ አባላት የጣት አሻራም ይወሰዳል።የጣት አሻራው ወደ አውሮፓ ማእከላዊ የዩሮዳክ (EURODAC) ዳታቤዝ እንዲገባ ይደረጋል።ይህም የሚሆነው የደብሊን 3 የስምምነት ደንብን ውጤታማ በሆነ መንገድ ተግባራዊ ለማድረግ ያለመ ስለሆነ ነው።

የደብሊን 3 የስምምነትን ደንብን የሚተገብሩት የአውሮፓ አገራት 27 ናቸው። (ኦስትሪያ ፣ ቤልጂየም ፣ ቡልጋሪያ ፣ ፈረንሳይ፣ ጀርመን፣ ዴንማርክ ፣ ግሪክ ፣ ኢስቶኒያ ፣ አየርላንድ፣ ስፔን ፣ጣሊያን፣ ክሮ ኤሽያ፣ ቆጵሮስ፣ ሊትዋንያ፣ላትቪያ፣ ሉዘምቤርግ ፣ ማልታ፣ ሆላንድ ፣ ሃንጋሪ ፣ ፖላንድ ፣ፖርቹጋል ፣ሮማኒያ ፣ስሎቫኪካ ፣ስሎቫኒያ ፣ስዊድን፣ ቼክ ሪፐብሊክ እና ፊንላንድ ናቸው:: እንዲሁም 4ቱ የትብብር አገራት [ስዊዘርላንድ፣ አይስላንድ ፣ ሊይችቴንስቴይን እና ኖርዌይ] ናቸው::

ዩናይትድ ኪንግዶም ከብሬግዚት በኋላ  እስከ 31 / 12 / 2020 ድረስ የቀረቡ የስፖንሰርሺፕ ማመልከቻዎችን ብቻ ለማስተናገድ ቃል የገባች ሲሆን፣ አዳዲስ ተመሳሳይ ማመልከቻዎችን ማቅረብ ከአሁን በኋላ አይቻልም ።

## በሌላ  የአውሮፓ ሀገር የሚገኝ የቤተሰብ አባል ወይም ጥገኛ  እና ሰብአዊነትን የሚመለከቱ ምክንያቶች

ለአቅመ አዳም/ሄዋን ያልደረሱና ያለ አጃቢ ብቻዎትን ከሆኑ እንዲሁም የቤተሰዎ አባላት (ወላጅ ፣እህት ወንድም ፣አክስት አጎት ፣አያቶች) በሌላ የደብሊን የስምምነት ደንብን በፈረመ

የአውሮፓ አገር ውስጥ በህጋዊ መንገድ የሚኖር ከሆነ፣ ማመልከቻዎትን የመመርመር ኃላፊነት ያለበት ሀገር ይህ የቤተሰብዎ አባል  የሚኖርበት አገር  ነው። ይህም የሚሆነው ለእርስዎ የሚጠቅም ሆኖ ከተገኘ ነው።  ጠቃሚ መሆኑ የሚመዘነው በገፆቹ መጨረሻ በሚገኘው ፎርም ላይ ተወካይዎ የሞላውን መረጃ መሰረት በማድረግ ነው።

ለአቅመ አዳም/ሄዋን ያልደረሱና ያለአጃቢ ብቻዎትን ከሆኑ፣ እንዲሁም ደግሞ በሌላ የደብሊን 3 የስምምነት ደንብን በፈረመ የአውሮፓ አገር የሚገኝ ማንኛውም የቤተሰብ አባል ከሌልዎ ማመልከቻዎን የሚመረምረው ግሪክ አገር ይሆናል።

ለአቅመ አዳም/ሄዋን የደረሱና የቤተሰብዎ አባል የሆነ ሰዉ ከላይ ከተዘረዘሩት አገር ውስጥ ጥገኝነት አግኝቶ የሚኖር ከሆነ፣ የእርሶን ማመልከቻ የመመርመር ኃላፊነት ያለበት አገር ቤተሰብዎ የሚኖሩበት አገር ይሆናል :: ይህም ሊሆን የሚችለው ሁለቱም ወገን የሚፈልጉት ከሆነ ነው። የዝምድናው ትስስር የተፈጠረው በትውልድ ሀገርዎ ወይም በሌላ ቦታ ሊሆን ይችላል።

ለአቅመ አዳም/ሄዋን የደረሱ ከሆነና ከላይ ከተጠቀሱት አገራት ውስጥ የጥገኝነት ማመልከቻ አቅርቦ በመጠባበቅ ላይ ያለ የቤተሰብ አባል ካልዎትና የዝምድናችሁ ትስስር ከትውልድ አገርዎ ጀምሮ የነበረ ከሆነ፣ የእርስዎን የጥገኝነት ጥያቄ የመመርመር ኃላፊነት ያለበት ይህ የቤተሰብዎ አባል የሚኖርበት አገር ነው። ይህም ሊሆን የሚችለው ሁለቱም ወገን የሚፈልጉት ከሆነ ነው።

**የሚከተሉት እንደ የቤተሰብ አባላት ይቆጠራሉ።**

- ባል ወይም ሚስት፣ ያልተጋቡና በእጮኝነት የሚኖሩ (ይህ ተቀባይነት የሚያገኘዉ ጉዳዩን የያዘው መንግስት ህግ ከሦስተኛ አገር የመጡ ያልተጋቡ እጮኞችን ከተጋቡ ሰዎች ጋር በተመሳሳይ ሁኔታ የሚመለከት ከሆነ ነው :: )
- ለአቅመ አዳም ያልደረሱ ያላገቡ ልጆች (ልጆቹ ያላገቡ መሆን ይኖርባቸዋል ።ነገር ግን ከትዳር ውስጥም ሆነ ከትዳር ውጪ የተወለዱ ልጆችን እንዲሁም ደግሞ በማደጎ ያደጉ ልጆችንም ያካትታል። )
- ለአቅመ አዳም/ሄዋን የደረሱ ከሆነና በእርግዝና ወይም በቅርብ ግዜ የወለዱ ከሆነና እንዲሁም ደግሞ በከባድ በሽታ ወይም በአካል ጉዳትና በዕድሜ መግፋት ምክንያት የልጅዎና የወንድምዎ እንዲሁም የወላጅዎ እርዳታ የሚያስፈልጎት ከሆነ፣ እርዳታውን የሚያቀርበው ግለሰብ በሌላ አገር አባል ውስጥ በህጋዊ መንገድ እየኖረ ከሆነ ይህ አባል አገር ከቤተሰብዎ አባል ጋር እንዲገናኙ ሊያደርግ ይችላል :: ይህ እንዲሆን የቤተሰባዊ ትስስራቹ ከትውልድ አገራችሁ ጀምሮ የነበረ ሊሆን ይገባል :: በተጨማሪም ይህ የእርስዎን እርዳታ የሚሻው ግለሰብ አስፈላጊውን እንክብካቤ የሚያገኝ ስለመሆኑ እርግጠኛ መሆን ያስፈልጋል። በተጨማሪም ሁለቱ ወገኖች በዚህ እንደሚስማሙ በፅሁፍ ፍላጎታቸውን መግለጽ ይኖርባቸዋል ።በተቃራኒው ደግሞ የእርሶን እርዳታ የሚሹና በህጋዊ መንገድ አባል በሆነ አገር ውስጥ የሚገኙ ልጆች፣ እህት/ወንድሞች እንዲሁም ደግሞ ወላጆች ካልዎት እርሶ ወደሚኖሩበት አገር መምጣት ይችላሉ።

ለጥገኝነት ማመልከቻዎ የመጀመሪያው ውሳኔ ከመውጣቱ በፊት ግሪክ አገር ጉዳይዎን የቤተሰብዎ አባል ወደ ሚገኝበት የአውሮፓ አባል አገር እንዲዛወር እና ከማንኛውም የቤተሰብዎ አባል ጋር እንዲቀላቀሉ ማድረግ ትችላለች። ይህም የሰብዓዊነት ፣ የቤተሰባዊና የባህላዊ ምክንያቶች መመዘኛዎችን እንዲሁም ደግሞ የሁለቱን ወገን ፍላጎት መሰረት በማድረግ ነው ::

## የመኖሪያ ፍቃድን፣ ቪዛን ፣ በህገ ወጥ መንገድ ወደ አንድ አገር ስለመግባት ፣ አባል በሆነ አገር ከዚህ ቀደም ስለመኖርዎና ቀደም ብሎ የቀረበ የጥገኝነት ማመልከቻን በተመለከተ

(በአገልግሎት ላይ ያለ ወይም ቀነ ገደቡ ካለቀ ከ2 ዓመት ያነሰ) የመኖርያ ፍቃድ ካሎት፣ በደብሊን የስምምነት ደንብ መሠረት ለአለም አቀፍ ጥበቃ ያቀረቡትን ማመልከቻ የመመርመር ኃላፊነት ያለበት አባል አገር የመኖሪያ ፍቃዱን የሰጠው አገር ነው።

ቪዛ ካሎት (ማለትም በአገልግሎት ላይ ያለ ወይም ቀነ ገደቡ ካለቀ 6 ወር ያልሞላው ) በደብሊን 3 የስምምነት ደንብ መሠረት ለአለም አቀፍ ጥበቃ ያስገቡትን ማመልከቻ የመመርመር ኃላፊነት ያለበት አባል አገር ቪዛውን የሰጠዎ አገር ነው።

ከአንድ በላይ የመኖሪያ ፍቃድ ወይም ቪዛ ካሎት በደብሊን 3 የስምምነት ደንብ መሠረት ለዓለም አቀፍ ጥበቃ ያቀረቡትን ማመልከቻ የመመርመር ኃላፊነት ያለበትን አገር የሚወሰነው የመኖሪያ ፍቃዱ ወይም ቪዛው በአገልግሎት ላይ የሚቆይበትን ጊዜ እና የቀነ ገደቡ የሚያልቅበትን ጊዜ በመመርኮዝ ይሆናል ::

ወደ ግሪክ አገር ከመምጣትዎ በፊት በህገወጥ መንገድ ሌላ የአውሮፓ አባል አገር ገብተው ከነበረ፣ የአለም አቀፍ ጥገኝነት ጥያቄዎን የመመርመር ኃላፊነት ያለበት አገር ቀደም ብለው የገቡበት አገር ነው። ይህም የሚሆነው በመካከሉ አገሪቷን ለቀው ካልወጡ ነው። ይህ ሁኔታ በህገወጥ መንገድ ከገቡ ከአስራ ሁለት(12) ወራት በኋላ አይሰራም።

ማመልከቻዎን ከማስገባትዎ በፊት በሌላ የአውሮፓ አባል አገር ውስጥ ለአምስት ተከታታይ ወራት የኖሩ ከሆነ የአለም አቀፍ ማመልከቻዎን የሚመረምረው አገር ለ 5 ወራት የኖሩበት አገር ይሆናል።

ቪዛ ወደማይጠይቅ አባል አገር በህጋዊ መንገድ ገብተው ከሆነ፣ የአለምአቀፍ ጥበቃ ጥያቄዎትን የሚመለከተው ይህ የገቡበት አገር ይሆናል ::

ማመልከቻዎን ያስገቡት በአንድ የአውሮፓ አባል አገር የአለም አቀፍ የአየር ማረፊያ ውስጥ ከሆነ፣ የአለም አቀፍ ጥበቃ ማመልከቻዎን የመመርመር ኃላፊነት ያለበት አገር አየር ማረፊያው የሚገኝበት አገር ነው።

የአለም አቀፍ ጥበቃ ማመልከቻዎን ሌላ የአውሮፓ አባል አገር አቅርበው አገሪቷን ለ3 ወራት ላልበበዛ ግዜ ለቀው ወደ ሌላ አገር ካልሄዱና የማመልከቻዎ የመጨረሻ ውሳኔ ተቀባይነት ያላገኘ ካልሆነ እንዲሁም ደግሞ በዚህ አገር መፈፀም ያለባቸው አስፈላጊ ሂደቶች በሙላ ያልተጠናቀቁ ካልሆነ፣ የማመልከቻዎን ምርመራ ማከናወን ያለበት ይህ አባል አገር መሆን አለበት።

## ⚠ ማሳሰቢያ

ከላይ የተጠቀሱት ነጥቦች ከርሶ ግላዊ ጉዳይ ጋር የማይገናኙ ከሆነ፣ ማመልከቻዎን የመመርመር ኃላፊነት ያለባት አገር ግሪክ ናት::

## ሌላ የደብሊን 3 የስምምነት ደንብን የፈረመ አገር ማመልከቻዎትን የመመርመር ኃላፊነት ካለው

ከላይ በተጠቀሰው መሠረት ማመልከቻዎትን የመመርምር ኃላፊነት ያለበት ሌላ የአውሮፓ አባል አገር ከሆነ እና የአለም አቀፍ ጥበቃ ማመልከቻዎን ለመመርመር ፈቃደኛ ከሆነ በግሪክ አገር ያቀረቡት ማመልከቻ ተቀባይነት ያላገኘ በመባል ይሰረዛል። በመቀጠል ማመልከቻዎን ይህ አባል አገር ለመመርመር ጥያቄዎን ከተቀበለበት ግዜ ጀምሮ በ6 ወር የግዜ ገደብ ባለው ውስጥ በህጉ መሠረት ወደ አገሪቷ ይዛወራሉ።

ይህን ውሳኔ ለመቃወም ወደ ይግባኝ ባለስልጣን በመቅረብ ይግባኝ የመጠየቅ መብት አልዎት። የይግባኝ ጥያቄዎን የጥገኝነት ቢሮ ወይም ውሳኔው ወደ ወጣበት ራሱን የቻለ የጥገኝነት ቢሮ በመቅረብ በውሳኔው ላይ በተፃፈው ቀነ ገደብ መሠረት ይግባኝ ማቅረብ ይችላሉ።

## አስፈላጊ መረጃዎች

ከላይ የተዘረዘሩትን መመዘኛዎች በተሳካ መልኩ በስራ ላይ ለማዋል የአለም አቀፍ ማመልከቻዎትን በሚያቀርቡ ጊዜ ለጥገኝነት አገልግሎቱ የሚከተሉትን ያሳውቁ።

1) ከሌላ አባል አገር የቆንስላ ባለስልጣን የተሰጥዎት ቪዛ(visa) ካሎት
2) የሌላ አባል አገር የመኖሪያ ፍቃድ ካሎት
3) ወደ ግሪክ አገር የገቡት በህገወጥ መንገድ በሌላ አባል አገር አቋርጠው ከሆነ
4) ወደ ግሪክ አገር ከመምጣትዎ በፊት ሌላ አባል አገር ኖረው ከሆነና ኖረው ከሆነ ደግሞ ለስንት ጊዜ እንደቆዩ
5) ሌላ የቤተሰብዎ ኣባል በሌላ አባል አገር የሚኖሩ ከሆነና እንዲሁም ደግሞ በምን አይነት ወረቀት እንደሚኖር ይግለጹ ።

በእጅዎ የሚገኙ ማንኛውም አይነት የማረጋገጫ ሰነዶች ማቅረብና አስፈልላጊ የሆኑ መረጃዎችን ሁሉ ማሳወቅ ይኖርቦታል። (ለምሳሌ: የጥገኝነት ጠያቂ ካርድ፣ የእርሶም ሆነ የቤተሰብዎ አባላት የመኖርያ ፈቃድ ፣ የቤተሰብዎን ሁኔታ የሚገልፅ ምስክር ወረቀት ወይም ሌሎች የምስክር ወረቀቶችና ቪዛዎች። ሌላ አገር እንደነበሩ የሚያረጋግጥ ማንኛውም አይነት ሰነዶች ለምሳሌ :የመጓጓዣና የሆቴል ደረሰኞች፣ የቤት ኪራይ ውሎችና ወ.ዘ.ተ ሊሆኑ ይችላሉ::)

## ✆ ከብሄራዊ የደብሊን ክፍል ጋር ለመገናኘት

ለተጨማሪ መረጃዎች ከብሄራዊ የደብሊን ክፍል ጋር መገናኘት ይችላሉ።

ከሰኞ እስከ አርብ በፈንጆቹ አቆጣጠር ከጠዋቱ 10 ሰዓት እስከ ጠዋት 12 ሰዓት በስልክ ቁጥራችን: 213-1629157 መደወል ይችላሉ። የመግባቢያ ቋንቋ ግርክኛ እና እንግሊዝኛ ብቻ

ሲሆን፣ ሲደውሉ የጉዳዩን የፋይል ቁጥር ማወቅ ይኖርበታል።ይህ ቁጥር የጥገኝነት ጠያቂ ካርድዎ ላይ ተጽፎ ይገኛል።

እንዲሁም በኢሜል አድራሻችን as.dpt.ndu@migration.gov.gr መልዕክት መላክ ይችላሉ :: መልዕክቱ በግሪክኛ ወይም በእንግሊዝኛ ሊሆን ይገባል። መልዕክትዎን ሲልኩ የጉዳዮን ቁጥር ርእስ (subject) በሚለው ቦታ ላይ ይጻፉ። የጉዳዮ ቁጥር የጥገኝነት ጠያቂ ካርዎ ላይ ተጽፎ ይገኛል።የካርድዎን ኮፒም አያያዘው ይላኩ ።

**በደብሊን ደንብ መሰረት ብቻቸውን ለሆኑና አጃቢ ለሌላቸው ለአቅመ አዳም/ሄዋን ላልደረሱ ልጆች የተሻለ ጥቅም እንዲያገኙ የሚረዳ ግምገማ**

ለአቅመ አዳም/ሄዋን ያልደረሱና ብቻቸውን ሆነው አጃቢ የሌላቸውን ልጆች ከቤተሰቦቻቸው ጋር የመገናኘት ፍላጎት ማመልከቻን ለማቀላጠፍ የተዘጋጀ አዲስ መገልገያ።

በዚህ መልኩ የደብሊን ደምብን 604/ 2013 አማካኝ በማድረግ የቤተሰብ ማገናኛ ማመልከቻ ሂደትን የተቃለለ በማድረግ፣ ብሄራዊ የደብሊን ክፍል ለአቅመ አዳም/ሄዋን ያልደረሱ ልጆችን የተሻለ ጥቅም እንዲያገኙ ግምገማ ለማድረግ አዲስ መገልገያ በስራ ላይ አውሏል፡

የዚህ መገልገያ አላማ ሌሎች አባል አገራት የቤተሰብ ማገናኛ ማመልከቻዎችን በሚመረምሩበት ጊዜ የሚጠይቋቸውን አስፈላጊ መረጃዎችን በሙሉ በአንድነት ለማሰባሰብ ነው።

ይህንን መገልገያ ለመስራት UNHCR፣ UNICEF እና EASO የተሳተፉ ሲሆን፣ ብሔራዊ የደብሊን ክፍል ደግሞ ቀደም ሲል የነበሩትን መገልገያዎች እንዲሁም ከተለያዩ መንግስታዊ ካልሆኑ ድርጅቶች የወጡ ጽሁፎችን ግምት ውስጥ በማስገባት ተጠቅሟል።

የደብሊን ብሄራዊ ክፍል የሆነውን የተሻለ ጥቅም የተሰኘውን ፎርምና መመሪያዎች እንዲሁም ደግሞ ቼክ ሊስት በ Word ወይም በpdf መልኩ ማውረድ ከፈለጉ http://migration.gov.gr/en/gas/diadikasies/doyvlino-iii/ የሚለውን ድረ-ገጽ ይጎብኙ::

ለተጨማሪ መረጃዎች እባከዎን ከታች በተጠቀሰው ድረገፅ ከደብሊን ክፍል ጋር ይገናኙ። as.dpt.ndu@migration.gov.gr

**መረጃዎች:**

ብሔራዊ የደብሊን ክፍል
አድራሻ: ሌኦፎሮስ ቲቮን 196-198፣ ኬራኒ ህንፃ፣ ሁለተኛ ፎቅ፣ 182 33
ስልክ: (0030)213-1629157(እንደ ፈረንጆቹ አቆጣጠር ከጠዋቱ 10:00 ሰዓት- ጠዋት 12:00 ሰዓት )
ኢሜል: as.dpt.ndu@migration.gov